አፍሪካ ቲቪ

12

# አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

www.AfricaAcademy.com

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት አዝካር ፣ ዱዓዕ እና ከፍተኛ ምንዳ ያላቸው ሥራዎች 5

በቴሌግራም

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

| | ተግባሩ | ከነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) የተነገረለት መረጃው |
|---|---|---|
| 56 | ወደ ቤት ሲገባም ሆነ በምግብ ጊዜ ቢስሚላህ ያለ ሰው | ወደቤቱ ሲገባና ሲመገብ አላህን ያወሳ ሰው ሰይጣን (ለባልንጀሮቹ)፡- ማደሪያም ሆነ እራት የላችሁም ይላል፡፡ ሲገባ አላህን ከላወሳ ደግሞ፡- ማደሪያ አገኘታችኋል ይላል፡፡ ሲመገብም አላህን ካላወሳ፡- እራትም አገኘታችኋል ይላል፡፡ |
| 57 | ከምግብ፣ ከመጠጥና ከአዲስ ልብስ በኋላ አልሀምዱ ሊላህ በማለት አላህን ያመሰገነ | ምግብን በልቶ (አልሐምዱሊላሂለዚ አጥዐመኒ ሀዛ ወረዘቀኒሂ ሚን ገይሪ ሐውሊን ሚኒ ወላቁወህ) ያለ ሰው ያለፈ ወንጀሉ ይሰረዝለታል፡፡ የሚጠጣ ነገር ጠጥቶ (አልሐምዱሊላሂለዚ ሰቃኒ ሀዛ፣ አዲስ ልብስ ሲለብስ (አልሐምዱሊላሂለዚ ከሳኒ ሀዛ) ያለ ሰውም እንዲሁ፡፡ |
| 58 | አላህ የስራውን ክብደት እንዲያቃልልለት የፈለገ | ፋጢማ፡- ሰራተኛ ይሰጠኝ፣ ብላ ነብዩን ስትጠይቅ ለእሷና ለዐሊይ፡- (ከጠየቃችሁኝ የሚሻል ነገር ልንገራችሁን? ከመኘታችሁ ላይ ስትሆኑ ሰላሳ አራት ጊዜ አላሁ አክበር፤ ሰላሳ ሶስት ጊዜ ሱብሀነላህ፤ ሰላሳ ሶስት ጊዜ አልሐምዱሊላህ፤ ማለት ከሰራተኛ ይሻላችኋል፡፡) አሏቸው፡፡ |
| 59 | ከግብረ-ስጋ ግንኙነት በፊት ዱዓ ያደረገ | ከሚስቱ ጋር ግንኙነት ማድረግ ሲፈልግ (ቢስሚላህ አላሁመ ጀኒብና ሸይጧን ወጀኒቢ ሸይጧን ማረዘቅተና) ያለ በዚያ ዕለት ልጅ ቢፈጠር ሰይጣን ለዝንት ዐለም አያጠቃውም፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| 60 | ሴት ልጅ ባሏን ማስደሰት | አምስት አወቃት ሶላቷን የሰገደች፤ ወሯን የፆመች፤ ብልቷን የጠበቀችና ባሏን የጠበቀች ሴት ከጀነት በሮች በፈለገሺው በር ግቢ ትባላለች፡፡ (ባሏ እንደተደሰተባት የሞተች ሴት ጀነት ትገባለች) |
| 61 | ዝምድናን መቀጠል | ሲሳዩ እንዲሰፋለትና ፋናው እንዲቆይለት የፈለገ ሰው ዝምድናን ይቀጥል፡፡ |
| 62 | የቲምን ማሳደግ | እኔና የቲም አሳዳጊ በጀነት ውስጥ እንደዚህ ነን ብለው አመልካች ጣታቸውንና መካከነኛ ጣታቸውን በአንድ አድርገው አሳዩ፡፡ |
| 63 | ጥሩ ስነ ምግባር | (ሙዕሚን በጥሩ ስነ ምግባር የፆመኛንና የትክክለኛ ሰጋጅን ምንዳ ያገኛል) (ባህሪያቸውን ለመሚያሳምሩ ሰዎች በከፍተኛው የጀነት ማዕረግ ውስጥ ቤት እንዳላቸው አብስር፡፡) |
| 64 | ለህዝቦች ማዘን | አላህ ከባሮቹ ሁሉ የሚወደው ሰው አብዛኛችን ነው፡፡ በምድር ላይ ያሉትን ሕዝቦች እዘኑላቸው፡፡ በሰማይ ያለው ያዝንላችኋል፡፡ |


AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

| | | |
|---|---|---|
| 65 | ለሙስሊሞች ጥሩ ነገሮችን መውደድ | ከናንተ አንዳችሁ ለራሱ የሚወደውን ለወንድሙ እስካልወደደ ድረስ አመነ አይባልም፡፡ |
| 66 | አይን አፋርነት | አይነ አፋርነት ኸይር ይዞ ነው የሚመጣው፡፡) (አይነ አፋርነት ከእምነት ነው፡፡) (አራት ነገሮች ከነቢያት ሱና ናቸው ሽቶ፣ አይነአፋርነት፣ ሲዋክና ጋብቻ) |
| 67 | በሰላም መቅደም | አንድ ሰው ወደ ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ መጥቶ:- አሰላሙ ዐለይኩም ሲል (አስር) አሉ፡፡ ሌላ ሰው መጠቶ:- አሰላሙዐለይኩም ወረህመቱላህ ሲል (ሀያ) አሉ፡፡ ሌላ ሰው መጥቶ:- አሰላሙ ዐለይኩም ወረህመቱላሂ ወበረካቱሁ ሲል (ሰላሳ) አሉ፡፡ (ምንዳ ማለት ነው፡፡) |
| 68 | ሲገናኙ መጨባበጥ | ሁለት ሙስሊሞች ተገናኝተው አይጨባበጡም፡ ከመለያየታቸው በፊት ወንጀላቸውን የተማሩ ቢሆን እንጂ፡፡ |



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

| | | |
|---|---|---|
| 69 | የሙስሊም ወንድሙ ክብር ሲነካ መከላከል | ከወንድሙ ክብር የተከላከለ ሰው አላህ የቂያማ እለት ከፊቱ እሳትን ይከላከልለታል። |
| 70 | መልካም ሰዎችን መውደድና ከእነሱ ጋር መቀማመጥ | (አንተ ከወደድከው ጋር ነህ) አነስ እንደሚሉት የነቢዩ ሱሃቦች በዚህ ሐዲስ የተደሰቱትን ያህል በምንም ተደስተው አያውቁም። |
| 71 | ለአላህ ክብር ሲሉ የተዋደዱ ሰዎች | አላህ (ለእኔ ብለው የተዋደዱ ሰዎች የብርሃን ወንበር አላቸው። ነቢዮችም ሆኑ ሰምአታት የሚቀኑባቸው ናቸው።) |
| 72 | ለሙስሊም ወንድሙ ዱዓ ማድረግ | ለወንድሙ በርቀት ላይ እያለ ዱዓ ያደረገለት ሰው ለእሱ የተወከለው መላይካ:- ኣሚን ለአንተም ተመሳሳዩ ይገባህ፣ ይለዋል። |
| 73 | ለወንድም ሆነ ለሴት አማኞች ምህረትን መለመን | ለወንድም ሆነ ለሴት አማኞች ምህረትን የለመነ ሰው በያንዳንዱ አማኝ ሰው አንዲት ሐሰነህ አለችው። |